# የኮሌራ በሽታ መንስኤውና መከላከያው

ኮሌራ ‹‹ቪብሪዮ ኮሌራ›› በሚባል መርዛማ ባክቴሪያ የሚመጣ የአንጀት ኢንፌክሽን ሲሆን አጣዳፊ ተቅማጥ የሚያስከትል በሽታ ነው፡፡ እንደ የአለም ጤና ድርጅት መረጃ በአለም ዙሪያ ከ1 ነጥብ 3 እስከ 4 ሚሊዮን የሚገመቱ ሰዎች በየአመቱ በኮሌራ እንደሚያዙና ከእነዚህም መካከል ከ21ሺ እስከ 143ሺ የሚደርሱ ሰዎች ደግሞ በዚህ በሽታ ለሞት ይዳረጋሉ፡፡

ኮሌራ የሚተላለፈው በኮሌራ ባክቴሪያ የተበከለ ውሃ በመጠጣት ወይም ምግብ በመመገብ ሲሆን ይህም የሚከሰተው የምንጠቀመው ውሃና ምግብ በበሽታው በተያዘ ሰው ሰገራ ሲበከልና የውሃ እጥረት እና የንፅህና ጉድለት ባለባቸው ቦታዎች የመከሰቱና የመዛመት እድሉ ሰፊ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ የኮሌራ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ምልክት ሊያሳዩም ላያሳዩም ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን በኮሌራ በሽታ ከተያዙ 10 ሰዎች መካከል አንዱ ከባድ ምልክት ሊያሳይ እንደሚችል መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

አንድ ሰው የተበከለ ምግብ ከበላ ወይም ውኃ ከጠጣ በኋላ በኮሌራ በሽታ መያዙን ምልክቶቹን ለማሳየት ከ12 ሰዓት እስከ 5 ቀናት እንደሚፈጅበት የጤና ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በኮሌራ በሽታ የተያዘ ሰው የሚያሳያቸው ምልክቶች በዋናነት ተቅማጥ፣ ማቅለሽለሽ እና ትዉከት፣ ፈሳሽ ማጣት፣ የአፍ መድረቅ፣ የአይን መሰርጎድ፣ የእንባ መድረቅ፣ የሽንት መቀነስ፣ የቆዳ መሸብሸብና አጠቃላይ የሆነ የድካም ስሜት እንደሚኖረው የአለም የጤና ድርጅት መረጃ ያስረዳል፡፡ በኮሌራ በሽታ የተያዘ ሰው ተቅማጡና ትውከቱ ቀጣይነት ያለው ከሆነ ከፍተኛ የሆነ የሰውነት ፈሳሽ መሚጠጥ፣ ፈጣን የልብ ምት፣ ዝቅተኛ የደም ግፊት፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ የኩላሊት መጎዳት፣ ያለመነቃቃት እና ሞት ሊያስከትል ይችላል፡፡

አብዛኛዎቹ በኮሌራ በሽታ የተያዙ ሰዎች አልፎ አልፎ የሆድ ቁርጠት ቢኖራቸውም ትኩሳት ግን አይስተዋልባቸውም፡፡ የኮሌራ በሽታን በዋናነት በላብራቶሪ በሚደረግ የሰገራ ምርመራ መለየት የሚቻል ሲሆን የላብራቶሪ ምርመራ በሌለባቸው አካባቢዎች ደግሞ የአለም ጤና ድርጅት ባወጣው መስፈርት መሰረት ታካሚው በሚያሳያቸው ምልክቶች እና በአካባቢው ባለው የበሽታው ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት ህክምና ማድረግ እንደሚቻል ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

አንድ ሰው በኮሌራ በሽታ ከተያዘ የሰውነት ፈሳሹ በፍጥነት ሊሚጠጥ ስለሚችል ፈሳሽ በመውሰድ መተካት አስፈላጊ ነው፡፡ የሕክምና እርዳታ እስከሚያገኙ ድረስ ኦ አር ኤስ (ORS) መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

ኮሌራ በልጆችም ሆነ በአዋቂዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከመሆኑም በላይ በበሽታው ተይዘው ከፍተኛ ተቅማጥ ያለባቸው ሰዎች ሕክምና ካልተደረገላቸው በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ሊገድላቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ቶሎ ሕክምና ከተደረገላቸው አብዛኛውን ጊዜ ዘላቂ ጉዳት ሳያስከትልባቸው ከበሽታው መዳን እንደሚችሉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ የኮሌራ ዋነኛው ህክምና የሰውነትን ፈሳሽን መተካት ስለሆነ ይህም

በኦ አር ኤስ ORS አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በደም ስር በሚሰጡ ፈሳሾች የሚከናወን ሲሆን ከባድ ምልክት ላለባቸው ሰዎች ፀረ-ባክቴሪያ መድሀኒቶች ሊሰጡ ይችላሉ። ከ5 አመት በታች ላሉ ህፃናት የዚንክ እንክብል የሚሰጣቸው ሲሆን ይህም የበሽታውን ጊዜ ለማሳጠር እና ከሌሎች የተቅማጥ በሽታዎች ለመከላከል ያግዛቸዋል።

የኮሌራ ህሙማን አብዛኛውን ጊዜ ከህመማቸው ካገገሙ በኋላ የኮሌራ ባክቴሪያ ተሸካሚዎች ባይሆኑም እንደገና ለበሽታው ከተጋለጡ የመታመም እድላቸው የሰፋ ነው። የኮሌራ በሽታን ለመከላከል ንፁህ ዉሃ መጠጣት እና መጠቀም፣ እጆዎን በሳሙና በንፁህ ዉሃ መታጠብ፣ መጸዳጃ ቤቶችን በመጠቀምና የሽንት ቤት ንፅህናን መጠበቅ ባክቴሪያው እንዳይሰራጭ ለመከላከልና ውኃንና ምግብን እንዳይበክል በጥንቃቄ ማስወገድ፣ ምግብን በመቀቀል ማብሰል እንዲሁም ንፅህናዉን በመጠበቅ፣ ሁልጊዜ ውሃን አፍልቶ እና አቀዝቅዞ መጠጣት ወይም በውሃ ማከሚያ ኬሚካል የታከመ ውሃ መጠቀም፣ የአካባቢ ንፅህናን በአግባቡ መጠበቅ፣ ምግብን በሚገባ አብስሎ በትኩስነቱ መመገብ በተጨማሪም ከቤት የሚወጡ ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻ የአካባቢን ዉሃን እንዳይበክሉ በአግባቡ ማስወገድ ተገቢ ነዉ። በመጨረሻም የበሽታዉ ምልክት የታየባቸዉ ህመምተኞች ፈጥነዉ ወደ ህክምና ተቋም በማምጣት ሊታከሙ ይገባል።

**ምንጭ፡- የአለም ጤና ድርጅት**